# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# ኢሳያስ ወደፊት ያለውን ያያል፡፡




ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ኢሳያስ ነብይ ነበረ ፤ የእርሱ ስራ እግዚአብሔር ምን እንደሚል ለሰዎች መናገር ነው፡፡ ሰዎች ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አይፈልጉም ፤ ነገር ግን ኢሳያስ እግዚአብሔርን ዝቅ የሚያደርግ አልነበረም፡፡ ኢሳያስ በአራት የተለያዩ ነገስታት ዘመን የሰበከ ሰው ነው ፤




ንጉስ ኦዚያ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ያለውን የይሁዳን ምድር ገዝቷል፡፡ በመጀመሪያ ፣ ኦዚያ በእግዚአብሔር ፊት መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ስለነበረ እግዚአብሔር ባረከው፡፡ ነገር ግን ኦዚያ መታበይ በመጀመሩ ምክንያት እግዚአብሔርን መታዘዝ አቆመ፡፡ ለምጣም በመሆኑም ምክንያት፣ እስኪሞት ድረስ ብቻውን ኖረ፡፡
UZZIAH
3
ንጉስ ኦዚያ ከስድሳ በላይ ለሆኑ አመታት ነግሷል፡፡ ሲሞት ፣ ልጁ ኢዮአታም ቦታውን ወስዶት ለአስራ ሰባት አመታት ነገሰ፡፡ እግዚአብሔር በኢሳያስና በሌሎች ነብያት ይናገር የነበረውን ነገር ይሰማ ስለነበረ ፣ እግዚአብሔር ኢዮአታምን ባረከው፡፡
4
የንጉስ ኢዮአታም ልጅ አካዝ ይባላል፡፡ አካዝ ሊነግስ ሲጀምር እድሜው ሃያ ነበረ ፤ እናም አስራ ስድስት አመታትን በኢየሩሳሌም ውስጥ ነገሰ፡፡ አካዝ ስለ እግዚአብሔር ግድ የማይሰጠው ሰው ነበረ፡፡ ጣኦታትንና ሴት አማልክትን ያመልክ ነበረ ፤ ሌሎች የእግዚአብሔር ሕዝብን ወደዚህ ድርጊት ይመራ ነበረ፡፡ ምንም እንኳን ኢሳያስ ቢያስጠነቅቀውም ፣ አካዝ የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ አይሰማም ነበረ፡፡ እርሱም በሰላሳ አምስት አመቱ ሞተ፡፡
5
እግዚአብሔርም ቀጥሎ የመጣውን ንጉስ ሕዝቂያስን ባረከው ፤ ምክንያቱም ጣኦታትንና የውሸት አማልክትን ሁሉ አስወግዶ ወደ እውነተኛው አምላክ ጸለየ፡፡ የጠላት ሰራዊት ይሁዳን ሲያጠቃ ፣ ሕዝቂያስ የእርሱ ሰራዊት ለማሸነፍ እጅግ ደካማ እንደሆነ አወቀ፡፡
6
ኢሳያስ ይሄንን መልእክት ለንጉሱ ላከለት ፤ “ይሔ እግዚአብሔር የሚናጋረው ነገር ነው ፤ እነዚህን ጠላቶች እንዳትፈራ፡፡.............እኔ እንዲወድቅ አደርገዋለሁ፡፡” ወዲያውም ፣ እግዚአብሔር የጠላት ሰራዊት ያለ ሕዝቂያስ ፍልሚያ እንዲሸሽ አደረገው፡፡
7
ምንም እንኳን በዙሪያው ያሉ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ብዙ የሚያውቁ ባይሆንም ፣ ኢሳያስ ግን ስለእርሱ ብዙ ያስብ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ፣ ራዕይን ተመለከተ ፤ ይህም ሳይተኛ የሚታይ ህልም አይነት ነው፡፡ በራዕዩም ፣ ኢሳያስ እግዚአብሔር እንዴት ያለ የከበረና ቅዱስ እንደሆነ ተመለከተ፡፡
8


በራዕዩም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ጠየቀ ፣ “ ማንን ልላክ;” ፡፡ “እኔ እዚህ አለሁ ፤ እኔን ላከኝ፡፡” እርሱም አግዚአብሔር የሚለውን ሁሉ ለማድረግና ወደ ሚልከው ቦታ ሁሉ ለመሔድ ዝግጁ ነበረ፡፡
9
ኢሳያስ ምንአልባት እግዚአብሔር ስለ እርሱ ሰምተው ወደ ማያውቁ በሩቅ ወዳሉ ሰዎች ሊልከው እንደሆነ አስቧል፡፡ ነገር ግን አይደለም ፤ እግዚአብሔር ያንን አላደረገም፡፡ እግዚአብሔር ኢሳያስን በራሱ ሐገር ላሉ ለራሱ ሰዎች እንዲናገር አዘዘው፡፡ እግዚአብሔር በኃጢያታቸው ምክንያት ማዘኑን መናገር ነበረበት፡፡
10
ኢሳያስ ለሕዝቡ መናገር የነበረበት ሌሎች ነገሮችም ነበሩ ፤ ጠንካራ አዳኝ ስለሆነው እና ከኃጢያታቸውና ከጠላቶቻቸው ሁሉ ሊያድናቸው ስለሚመጣው ሰው አስደናቂ ነገሮች፡፡
11
አይሁዳዊያን ሰዎች የሔንን ሰው “መሲህ” ብለው ይጠሩታል፡፡ ምንም እንኳን እነርሱ እግዚአብሔር መሲህን እንደሚልክላቸው ቢጠብቁም ፣ ብዙ ሰዎች ግን ሊመጣ እንደማይችል እያሰቡ ይኖሩ ነበረ፡፡
12
ኢሳያስ ስለ መሲሁ የተናገራቸው ነገሮች በአጠቃላይ በመጽሐፉ የተቀመጡ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህን ነገሮች ከመሆናቸው መቶ አመታት አስቀድሞ ተናግሮ ቢሆንም ፣ ኢሳያስ ስለመሲሁ ያለው ነገር ሁሉ እውነት ሆኖ ይታያል፡፡
BOOK OF THE PROPHET ISAIAH
13
ኢሳያስ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ራሱ ምልክትን ያሳያል፡፡
እርሱም ፣”እነሆ ድንግል ወንድ ልጅ ትወልዳለች ፤ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች፡፡” ሰዎቹ ፣ ኢሳያስ ስለ መሲሁ እየተናገረ መሆኑን አውቀዋል ፤ ምክንያቱም ፣
አንዲት ሴት ድንግል ሆና ልትወልድ እንደማትችል ያውቃሉ፡፡ በተጨማሪም ፣ አማኑኤል የሚለው ስም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው፡፡
14



“ልጅ ተወልዶልናል ፤ ወንድ ልጅም
ተሰጥቶናል፡፡ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ
ይሆናል፡፡ ስሙም ፣ ድንቅ፣ መካር ፣
ኃያል አምላክ ፣ የዘላለም አባት ና የሰላም
አለቃ ይባላል፡፡”ኢሳያስ የእግዚአብሔር
ቃል እውነት እንደሆነ እርግጠኛ ነበረ ፤
ሲናገርም ልክ የሆነ ያክል አድርጎ ነበረ፡፡
ይሔ ትንቢት ይባላል፡፡”

15

ኢሳያስ እንደሚለው ያ መሲህ ትልቅ እንደሚሆንና ትልቅ ነገሮችን
እንደሚያደርግ ነው፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር ለኢሳያስ መሲሁ መከራ
እንደሚቀበል እና እንደሚሞት ይናገር ነበረ፡፡ ኢሳያስም መሲህ እንዴት
በአንድ ጊዜ ታላቅና ኃይለኛ ከዚያ ደግሞ ደካማ እና የተጎዳ ሊሆን
እንደሚችል ሳይደነቅ አይቀርም፡፡ ነገር ግን
ኢሳያስ ከእግዚአብሔርጋ አልተሟገተም ነበረ ፤
እግዚአብሔር የነገረውን ብቻ ይደግም
ነበረ፡፡ ትንቢቱ እውነት እንደሚሆን
እግዚአብሔር ያረጋግጥለት ነበረ፡፡



16

መሲህ እየመጣ ነበረ ፤ ለአይሁድ ሕዝብ ብቻ ግን አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር
ለኢሳያስ እንደሚለው ፣ መሲሕ “ለአሕዛብ ሁሉ ብርሃን” እንደሚሆን ነበረ፡፡
አሕዛብ ከአይሁድ ሕዝብ ውጪ ያለ የአለም ሕዝብ ነው፡፡ እግዚአብሔር
ሁሉን ይወዳል ፤ መሲሁም ሁሉን ሊባርክና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መዳንን
የሚያመጣ ነው፡፡



17

ኢሳያስ ወደፊት ያለውን ያያል፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል**
**በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ኢሳያስ 1፣ 6፣ 7፣ 9 ፣ 53

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

18




27 60

19

**ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን**
**እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።**

**እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።**
**የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን**
**አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት**
**እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።**
**ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!**
**ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል**
**ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤**
**እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።**

**ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት**
**ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት**
**ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ**
**ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን**
**ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና**
**እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።**

**በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር!** **የሐ.** 3.16

20